የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፯
አዲስ አበባ – ሚያዝያ ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 47
ADDIS ABABA– 22nd April, 1999

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፷፮/፲፱፻፺፩ ዓ·ም
ለግብርና ምርምርና ሥልጠና ፕሮጀክት ከፊል ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ...................... ገጽ ፩ሺ፲፰

## CONTENTS

Proclamation No. 166/1999
International Fund for Agricultural Development Loan Agreement for Partly Financing the Agricultural Research and Training Project Ratification Proclamation ...................... Page 1018

## አዋጅ ቁጥር ፩፻፷፮/፲፱፻፺፩
## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለግብርና ምርምርና ሥልጠና ፕሮጀክት ከፊል ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ኤስ·ዲ· አር ፲፫ሚሊዮን፮፻፶ሺህ,, (አሥራ ሦስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃምሣ ሺህ ኤስ·ዲ·አር) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል እ·ኤ·አ ኖቬምበር ፲ ቀን ፲፱፻፺፰ በሮም የተፈረመ በመሆኑ፤

መሠረታዊ የኤኮኖሚ ዓለም አቀፍ ውሎች ተፈጻሚ ከመሆናቸው በፊት መጽደቅ ስላለባቸው፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዚያ ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም· ባደረገው ስብሰባው ያጸደቀው ስለሆነ፤

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ለግብርና ምርምርና ሥልጠና ፕሮጀክት ከፊል ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፷፮/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 166/1999
## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL FUND FOR AGRICULTURAL DEVELOPMENT

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Fund for Agricultural Development stipulating that the International Fund for Agricultural Development shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of SDR 13,650,000 (thirteen million six hundred fifty thousand Special Drawing Rights) for partly financing the Agricultural Research and Training Project, was signed in Rome on the 10th day of November, 1998;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 22nd of April, 1999;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "International Fund for Agricultural Development Loan Agreement for Partly Financing the Agricultural Research and Training Project Ratification Proclamation No. 166/1999."

፪. <u>ትርጓሜ</u>
በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ኖቬምበር ፲ ቀን ፲፱፻፺፰ በሮም የተፈረመው ቁጥር ፬፻፹ ኢት. የብድር ስምምነት ነው።

፫. <u>የገንዘብ ሚኒስትር ሥልጣን</u>
የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲፫ሚሊዮን ፮፻፶ሺህ ኤስ.ዲ.አር. (አሥራ ሦስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃምሣ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲያውል በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>
ይህ አዋጅ ከሚያዝያ ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፩ ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Definition*
In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement No. 480 ET signed in Rome on the 10th day of November, 1998 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Fund for Agricultural Development.

3. *Power of the Minister of Finance*
The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of SDR 13,650,000 (thirteen million six hundred fifty thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*
This Proclamation shall enter into force as of the 22nd day of April, 1999.

Done at Addis Ababa, this 22nd day of April, 1999.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE